# ሙሴ፡ በእምነት

አመሰግናለሁ፡ ወንድም ኔቪል እንደምን አደራችሁ፡ ወገኖች። ዛሬ በዚህ ድንኳን ውስጥ መሆናችን ጥሩ ነው። ምናልባት ዛሬ ጠዋት ወንድም ኔቪልን ከሰበከ፡ እኔ ዛሬ ማታ እሰብካለሁ ብየ ነበር። ከዚያ በኋላም ለዛሬ ጠዋት የሰንበት ትምህርት እየተዘጋጀሁ ነበር። ሌላም… እንደ ጌታ ፈቃድ፡ የሰንበትን ትምህርት——በዚህኛው እሁድ ለመማር እንሞክራለን።

2 ስለዚህ፡ አሁን፡ እዚህ ከመጣሁ፡ ሁለት ሳምንት ሞልቶኛል። እንናተም እንደምትረዱት፡ ወደ ወንጌል ስራ ሰወጣ፡ ምንም ማድረግ እስከሚሳነኝ ድረስ፡ እጅግ፡ እጅግ እደክማለሁ። ስለዚህ ትንሽ እረፍት ለመውሰድ መምጣት ስለ ነበረብኝ መጣሁ። ከዚያ በተወለድኩበት፡ ኬንታኪ ወደሚገኘው፡ ዋልፍ ክሪክ ወደተባለው ግድብ ለሶስት ቀናት ሄድኩኝ። ሳሰበው፡ "አሁን፡ በጣም ደስተኛ ሆኛለሁ። ደህና ነኝ።"

3 ከዚያ በኋላ ወደ ቤት ገብቼ፡ ከፊቴ የገጠመኝ የመጀመርያ ነገር የመንግሰት ግብር የሚመለከት ጉዳይ ነው። ከሰር እንደገና ወደኋላ ተመለሰኩኝ። ስለዚህ እረፍት ለማግኘት ገና አንድ ወይም ሁለት ሳምንት እንደሚፈጅብኝ አስተውያለሁ።

4 አገልግሎቴ የሚቀየርበት ጊዜ መጥቷል። በዚህም ምክንያት ምንም ዓይነት የጉባኤ ቀጠሮዎች አልያዝኩም። ዘና ብየ ተመልካች የሆንኩበት ምክንያት፡ ምናልባት፡ ለሚቀጥሉ ጥቂት ሳምንታት፡ አርፋለሁ፡ ፈጽሜ አርፋለሁ ጌታንም እጠብቃለሁ፡ ብየ ስላሰብኩ ነው።

5 እዚህ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ፡ በተለይም አንጋፋ-የሆናችሁ፡ እስከ አሁን ድረስ አብራችሁን ያላችሁ፡ ጌታ የገባልን ቃል አስታውሱ፡ አደርጋለሁ ያለውን ነገር ሁሉ አድርጓል።

6 ያኔ በመጀመርያ፡ በዚህ ቤተክርስትያን፡ የመሰረት ድንጋይ ባሰቀመጥንባት ማለዳ፡ የተናገረውን፡ ታስታውሳላችሁ… በድንጋዩ ላይ ተጽፎ፡ተቀምጧል፡ በመጽሃፍ ቅዱሴም በአንዱ-ገጽ ላይ ጽፌዋለሁ። በዚያች ማለዳ፡ ታላቁ ራዕይ፦ "ይህ ድንኳን የአንተ አይደለም፡" አለኝ።

7 "ጌታ ሆይ፡ ታዲያ የት አለ?" ከሰማያት በታች እንድዘጋጅ አደረገኝ። ድምጽም መጣ። ዓይኖቼን አንስቼ፡ ዛፍ እስከ ፍሬዎቻቸው፡ የመሳሰሉ፡ ሶስት መስቀሎችን አየሁ። ራዕዩን እናንተ ታውቃላችሁ። ለብዙ አመታት፡ ተጽፎ ቆይቷል።

8 በቀደምለት፡ እድሜ ጠገብ የሆነውን ማስታወሻ፡ አንስቼ፡ ጌታ አስቀድሞ ተናግሯቸው፡ የተፈጸሙ፡ አንዳንድ ነገሮችን አነበብኩ። የጦርነቱ አፈጻጸም፣ አሁን የተፈጸሙት ነገሮች፣ እና አስደናቂ በሆኑ ጉዳዮች በተመለከተ ነው።

9 ከእነዚያ ታላላቅ ትንቢቶች መካከል፡ ሁለት ያልተፈጸሙ ነገሮች ቀርቷል። አንደኛው፡ በሪሞት ኮንትሮል የምትሰራ፡ እንቁላል የምትመስል መኪና አስፋልት ላይ መውጣት ነው፡ እናንተ አትነዷትም። እራሷ ትቆጣጠረዋለች። ሁለተኛው ደግሞ አሜሪካ የሴቶች አገር ናትና፡ የታላቋ ሴት መምጣት ነው። ስለዚህ…

በምድሪቱ ላይ ታላቅ ሴት ትነሣለች፡ ሴቲቱም ፕረዚደንት ወይም የሆነ ነገር ትሆናለች። ከዚያ ቀጥሎ ፍጹም የሆነ ጥፋት ይመጣል። አገሪቱ ተጠራርጋ ትጠፋለች።

10 (ሴቲቱን፡ በሚመለከት፡ የተናገረው፡ ከጌታ ነው።) ቀጥሎ ያለውን፡ ግን፡ ጌታ የተናገረው አይደለም... የራሴ ግምት ነው። በ1933 ላይ ዓለም በ77 ላይ ፈጽማ ትጠፋለች ብየ፡ ግምቴን፡ ተናግሬአለሁና።

11 እኔ ያኔ፡ አሁን እንደታጠቁት ፈጽሞ የሚያጠፋ ነገር እንዳላቸው አላውቅም፡ ምድሪቱ ግን ፈጽማ ስትጠፋ አይቻታለሁ፡ የሚቀርላት፡ የዛፍ ግንድ እና የመሳሰለ ነገር ብቻ ነው።

12 ስለዚህ፡ ይሄም ይመጣል። የተናገራቸው ሁሉ እሱ እንዳላቸው ከተፈጸሙ፡ ይሄኛውም፡ በቅዱስ ቃል እንደተናገረው ነው፡ እሱ ያለው፡ ክርስቶስ አንደኛ ጊዜ ከመጣ፡ ሁለተኛ ጊዜም ይመጣል። ይሆናሉ ያላቸው ነገሮች ሁሉ ይፈጸማሉ። እኛ... ቤተክርስትያን የምትነጠቅበት ጊዜ አሁን እውቀን ስንመለከተው፡ እንደ አገር፡ ቁጥራችን ሊጠራ አሁን እጅግ ተቃርቧል። በምንወስድበት ቀን እና ወቅት እየኖርን እንዳለ ማወቃችን፡ የማንም አማኝ፡ እና የአገልጋይ ልብ ያነሣሣል። ይህም፡ የሰው ልጆች በምድር መኖር ከጀመሩ ጀምሮ፡ እጅግ ታላቅ የሚባል፡ የቤተ ክርስትያን ጊዜ፡ ይህ ጊዜ ነው። ስለዚህ፡ በትክክል ጸሎታችሁ ያስፈልገኛል።

13 ሌላም በጉባኤው እንዳየሁት፡ የሆነ ነገር እንዳለ አይቻለሁ... በቤተክርስትያን፡ አንዳንድ ቦርድ እና የመሳሰሉ፡ ዳግም-ምርጫ እና ወዘተ ይደረጋል።

14 ቤተክርስትያንም—ስብሰባ ቢጣ ያስፈልጋታል፡ መፐወዝ አለባት። እናንተ ለእኔ ዘወትር መልካሞች ናችሁ፡ በረከቴ ሆናችኋል። እኔም እዚህ በመምጣቴ፡ በረከት እንደሆንኩ ይሠማኛል። ለእኔ ግን ከእናንተ ጋር መሆኔ፡ በእርግጠኝነት፡ በረከት ሆኖልኛል። ከእግዚአብሄር እንዳየሁት፡ እኔ የነገርኳችሁ ነገሮች ሁሉ እውነት እንደሆኑ አርጋችሁ ተቀብላችኋል። በዚህም እኔ—አመሰግናለሁ።

15 ስለዚህ፡ ገብቼ፡ ቤተ ክርስትያናችን፡ ስለ ቦርዶቿ፡ እና ስለ ምርጫው የሚስተካከል ነገሮች ለማግኘት፡ መፈተሽ ያስፈልገኝ ነበር። ከዚያ—ከዚያም በኋላ፡ ወደ ወንጌል ስራ ከመውጣቴ በፊት፡ ሄጄ፡ ትንሽ እረፍት አገኛለሁ ብየ አሰብኩ።

16 ይህ ነገር፡ ወደ ውጪ አይወጣም። ለእናንተ ብቻ ያዙት። ለዚህች ጉባኤ ነው። በዚህ ጉባኤ ስብሰባ አስፈልጎናል፡ ይህም የተሳሳቱ ነገሮች ሁሉ፡ እና ሌሎች፡ ሲመላለሱብን የኖሩ ነገሮች፡ ምናልባትም አንዳችን ከሌላው ጋር ያሉ ትናንሽ ስሜቶች፡ ሁሉንም አውጥቼ፡ ፊት-ለ-ፊት እንዲጋፈጡ አደርጋቸዋለሁ። ይሄን መጋፈጥ ካልፈለጋችሁ፡ አገር ብትቀይሩ ይሻላችኋል፡ ምክንያቱ ድሮ በዚህች ጉባኤ እንደሚደረግ፡ አሁንም ከእያንዳንዱ ነገር ጋር ፊት-ለ-ፊት ልትጋፈጡ ነው። የክርስቶስን አካል፡ በበረከት ማዕድ ፊት የጌታ እራትን የናቅን ወንድማማቾች፡ እና እህትማማቾች ስለሆንን፡ ነገር ሁሉ መቃናት አለበት። ይህም ሰይጣን ያመጣው ስህተት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፡ ይህም የስሜት መቀያየር፣ መከፋፈልን ማምጣት፣ ወይም የመሳሰሉ ነገሮችን ይፈጥራል። ወንድማችን ኔቪልን ይዤ እሄዳለሁ፣ ከቦታ ወደ ቦታ እንሄዳለን፣ ሰዎችን ከሰዎች

ጋር፡ ወደ አንድነት እናቀራርባለን፡ የድሮዋ ጉባኤ ለእግዚአብሄር መንግስት መሰራት እስክትችል፡ እስክትጸና፡ እና በእግሮቿም እስክትቆም ድረስ እንሰራለን። ዛሬ ጠዋት፡ ይህ ነገር የትንሿ ጉባኤያችን ጉዳይ ነው፡ ያልኩበት ምክንያት፡ ይህ ነው።

17 እና አሁን ትንሽ እረፍት አግኝቼ፣ በተቻለኝ ፍጥነት እመለሳለሁ። ከዚያ እንደገና ወደ አገልግሎት እንድሄድ እጠብቃለሁ። እናም በዚህ ጊዜ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በመዋጮ ካጠራቀምነው እና ካለን ትንሽ ገንዘብ፡ከራሴም፡ ጭምር፡ በዚህኛው… ወደ ውጭ አገር የሚሽን ዕቅድ መውሰድ ፈልጌአለሁ። አንዳንድ አዳዲስ መሳርያዎች፡ እና አዲስ ድንኳን ገዝተን፡ ሜዳ ላይ እንጀምራለን። ከቸርች ወደ ቸርች አንሄድም፡ ነገር ግን በገዛ ቤተ ክርስትያናችን እናደርገዋለን።

18 ማለት፡ የጋበዙኝን ወንድሞች መናቄ አይደለም፡ መልካም ነገር ነው። ብዙ ጊዜ ግን፡ የሚዘጋጁ ኮንፈረንሶች ስታዩአቸው፡ አንተም ትመጣለህ፡ ወዳጆችህም ሁሉ ይኖራሉ ይሏችኋል፡ ከዚያ በኋላ ገንዘብን ፍለጋ ታላቅ ከበሮ ይጎሰምበታል። ሰዎችን እንደ መበዝበዝ ነው። አያችሁ፡ ይሄን መረዳት ጀምሬአለሁ። ስለዚህ ይህ—ይህ ትክክል አይደለም። እነሱን መሰብሰብ የሚያስችለን ሰፍራ ያስፈልጋል። ገንዘባችሁን ማምጣት አይጠበቅባችሁም። እናንተ፡ እራሳችሁ ብቻ፡ ኑና—መጥታችሁ ጌታን አገልግሉ። አያችሁ? ስለዚህ አሁን…

19 የእኔ አገልግሎት አሁን ተቀይሯል። ያኔ የሰዎችን እጅ ስይዝ ታስታውሳላችሁ፡ ይዤ እቆምና፡ ችግሮቻቸው ምን እንደሆነ ጌታ ይነግረኝ ነበር። “ከዚያ ቀጥሎ የሰዎች የልብ ምስጢር፡የምታውቅበት ጊዜ ይመጣል፡” ተባለልኝ። ልክ እንደተነገረኝ እየሆነ እንደሆነም ሁላችሁ ታውቃላችሁ። ይህ ነገር አስቀድሞ የተነገረ እና በትንቢት ተነግሮ የቆየ፡ ከሌሎቹ እጅግ የጠለቀ፡ ቀጣይ ስህበት ነው፡ አያችሁ። ስለዚህ በዚህ ቅጽበት በመቀየር ሂደት ይገኛል።

20 ለዚህም ነው ሰይጣን በገቢ ግብር የሚዋጋኝ፣ እንደ አገልጋይ የተቀበልኳት ሰባራ ሳንቲም ሳትቀር፡ ለመንግስት ግብር፡ ባለ ዕዳ ነህ፡ ሊለኝ ይሞክራል፡ ይህም አገልግሎት ከጀመርኩ ባሉት ሃያ-ሰባት አመታት ያለው ሁሉ ነው። ትክክል ግን አይደለም፡ ምክንያቱ በቤተ ክርስትያን ወጪ የተደረገ ነው።

21 ትክክለኛ ነገር ነው። እኔም የቤተ ክርስቲያኒቱ ባለአደራ ነኝና። መዝገብ ላይ ሰፍሯል። ስለዚህ፡ የዚህ ቤተ ክርስትያን ንብረት ያዥ-ባለአደራ፡ ከሆንኩ፡ እንግዲያውስ በምንም መመዘኛ… መንግስት ጣልቃ የሚገባበት ጉዳይ አይኖረውም። እነሱ ቤተ ክርስትያንን አይደለም የጠየቁት። የቤተ ክርስትያኒቱ ንብረት ያዥ የሆንኩትን እኔን ነው የጠየቁት። ሌሎች ባለአደራዎችም በባንክ ቤት ውስጥ ባለው ደብተር ፈርመውበታል፡ በርግጥ ለእኔ የተበረከተ ነበር… የግሌ ፋውንዴሽን ከማራመድ ይልቅ ግን፡ በቤተ ክርስትያን እንዲያልፍ አደረግኩት፡ በዚህ ይሁን በዚያ፡ ፋውንዴሽን መሆኑ የማይቀር ነውና።

22 እንዲህ በማድረጌም፡ ቤተ ክርስትያኒቱን ትቼ ከመሄድ እና ከመራቅ፡ ወጥቼም በዚህ ሰፍራ የሌለኝ ከመሆን ይዞኛል። ወደዚህ ቤተ ክርስትያን በየጊዜው እየመጣሁ፡ እንደማገዛቸው፡ ለህዝቡ ቃል ስለገባሁላቸው ነው። እናንተ ሰዎች ቃል ገብቼላችኋለሁና፡ እንዲህ ያደረግኩበት ምክንያት ይህ

ነው። የግል ጉዳይ ከማድረግ፡ በእንዲህ መልኩ ያደረግኩበት ምክንያት ይህ ነው። ከዚያ፡ በግል’ማ ካደረጋችሁት፡ ድርጅታዊ አካሄድ ይሆናል። እኔ ደግሞ ድርጅታዊነትን እጅግ እቃወማለሁ። ስለዚህ በእግዚአብሔር መንግስት መቀጠል እንድንችል፡ እኔ—እንዲሁ ባለበት፡ በእግዚአብሄር እጅ እተወዋለሁ።

23 ስለዚህ፡ ዛሬ ማለዳ፡ ይህ የተባረከና አንጋፋ ቃል መማር፡ እና ማመን እንሻለን።

24 በተጨማሪም፡ አሁን፡ እንዲህ ማለት እፈልጋለሁ... ወንድም ኢጋን እና ሌሎች ባለአደራዎች የሆኑት፡ ማታ ካደረግነው የባለአደራዎች ስብሰባ በኋላ፡ ተቀምጠው አይቻቸዋለሁ፡ እውነቱን ስንናገር፡ ከእንግዲህ እጩ ባለአደራ—አለመሆናችሁ በቤተ ክርስትያን ፊት እናገራለሁ። የተመረጣችሁ ባለአደራ ናችሁ፡ ስሞቻችሁም በመዝገብ ውስጥ ሰፍሯል። በጣም ጥሩ።

25 ከዚህም በመቀጠል አንዳንድ ሂደቶች እና—የዲያቆናት ምርጫ፡ ያካሂዳሉ። ስለዚህ ይህ ጉባኤ ካለቀ በኋላ፡ ወድያውኑ ወንድም ነቪል ባለአደራዎች እና ሌሎች፡ በጣም ጥሩ፡ ቤተክርስትያን ቦታ ቦታውን እንዳስያዝነው፡ ስሞቻቸውን ይጠራል። ድህረ ገጽ ሁሉ፡ ካስተካከልን በኋላ፡ እንደ አመጣጡ ሪቫይቫል ሊኖረን ይችላል።

26 እስኪ፡ ቀጣይ ገጾችን ከመግለጣችን በፊት፡ ስለ ታላቁና ህያው የአምላክ ቃል፣ ስለ ታላቁ የሰንበት ትምህርታችን፡ የመጽሀፉን ደራሲ እያነጋገርነው፡ ለጥቂት ደቂቃ፡ እራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። በረከት ሊያስከለክሏችሁ የሚችሉ ሐሳቦች፣ ወይም ተቃራኒ ነገሮች ሁሉ፡ ከራሳችሁ አስወግዱ።

እንጸልይ።

27 ቅዱስና ጻድቅ አምላክ ሆይ፣ ወደ ተባረከው የነሐሴ ህልውናህ አሁን ቀረብን፣ ህይወታችንን፡ እና—ነፍሳችን፡ እና አካላችን፣ እና አገልግሎቶቻችን እና ተሰጥኦዎቻችንን ሁሉ፡ ለአንተ እንሰጣለን። አለን የምንለው ሁሉ፡ ወደ አንተ እናቀርባለን። አንተም ስትመለከተን፡ ጌታ ሆይ፡ ራቁትና ያልተናዘዝነው ኃጢአት ካለብን፡ ጌታ አምላክ ሆይ፡ የልጅህን፡ የኢየሱስን ደም፡ እንዲህ ባለው ሰፍራ እንድትረጨው፡ እንለምንሃለን። ምክንያቱም፡ እኛ በራሳችን በቂ እንዳልሆንን ተረድተናል፡ ራሳችንን-ወደ መቻል መድረስ በፍጹም የማይቻለን ነን። ነገር ግን ዕዳችንን ለማስወገድ ሙሉ በሙሉ በክቡር ደሙ፡ እና በጸጋው ላይ እንደገፋለን፡ ይህም እኛ ሐጢአተኞች የኢየሱስ ክርስቶስን ደም በፊታችን ይዘን፡ አንድ ቀን ወደ ህልውናህ በድፍረት መቅረብ እንድንችል ነው። ይህም፡ ባለፋት ዘመናት፡ የአንድያ ልጅህ ደም እንደሆነ፡ አንተ እራስህ መሰክረህለታል፡ እንዲሁም፦ “በእሱ በኩል፡ ሐጢአቶቻችንን ብንናዘዝ፡ በጸጋው ትጸድቃላችሁ፡” ብለህ ቃል ኪዳን ገብተህልናል።

28 አሁንም ጌታ ሆይ፡ ማንኛውንም ስህተት፡ ማንኛውንም መተላለፍ፡ ወይም በስህተት ኃጢአት፡ በበደል፡ በክፉ የዲያብሎስ ፍላጻዎች ነፍሳችንን ክፉ አሳብ ከነካው፡ ይቅር እንድትለን እንጠይቃለን፡ የአንተ እና የህዝብህ ጠላት የሆነውን ይህ ክፉ፡ አስወግድልን።

29 እናም በዚህ ጊዜ ቃሉን እንዲቆጣጠር መንፈስ ቅዱስን እንድትልክ እንጠይቃለን፡ ቃልህን፡ በእኛ አልፈህ እንድትናገር፡ እና በእኛ እንድትሰማ፡ እራሳችንን እንደ መጠቀምያ አቀረብን። እኛም ዛሬ ከአንተ ዘንድ በምንቀበለው፡

በመንፈስ ቅዱስ ምክንያት፡ ስለ ክርስቶስ ጥሪ፡ ዳግም-መቃናታችንን ተቀብለን ከዚህ ሰፍራ ስንወጣ፡ ለዛሬ ማታ እና ለነገ አገልግሎት፡ የምንበቃ አድርገህን መመለስ ይሁንልን።

30 በዓለም ሁሉ ያለች ቤተክርስትያን፡ እና በየሰፍራው የሚገኙ ወንድሞቻችንን፡ በዚህ ክፉ ዘመን የህይወትን ቃል የያዙ ሁሉ ባርክልን። ጨለማው በፍጥነት እየመጣ ነውና፡ የምንሰራበት ብዙ ጊዜ እንዳልቀረን ይሰማናል። የሰልፍ ደመናዎች ዳግም ተንሳፈዋል። ክፋት ቀርቧል፡ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እንድንሰራ እንድትፈቅድልን እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ የደከመውን ሰውነታችንን አሳርፍ፡ እና ወደ ሰልፉ መልሰን። በጌታ በኢየሱስ ሰም እንለምነዋለን፡ ስለ እርሱም እንጸልያለን። አሜን።

31 ዛሬ ጠዋት፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ ከ—ዕብራውያን መጽሐፍ 11ኛው ምዕራፍ፡ እንከፍታለን።

32 ረቡዕ ምሽት ከዕብራውያን መጽሐፍ 7ኛው ምዕራፍ ላይ ተነጋግረናል፡ ስለ "መልከ ጸዴቅ፡ ያለ አባት፡ እና ያለ እናት፡ ለዘመኑም መጀመርያ፡ ወይም የህይወቱ ፍጻሜ የሌለው ስለመሆኑ።"

33 ምናልባትም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ይህን አሰደናቂ መጽሐፍ እንደገና መክፈት ተገቢ ነው ብዬ አሰብኩ፣ በባለፈው ምንባብ ውሰጥ፡ ለመናገር የምንፈልገውን ዳራዎችን አሰቀምጠናልና። 9ኛው ምዕራፍ፡ እና 10ኛው ምዕራፍ በመዝለል፡ እነርሱም ስለ መሰዋዕት ሕጎች ናቸው፡ ከዚያም አልፈን ወደ "እምነት" ደርሰናል። ስለዚህ አሁን በዕብራውያን መጽሐፍ፡ 11ኛው ምዕራፍ፡ ከቁጥር 23 ጀምረን፡ እንዲህ እናነባለን፦

> **ሙሴ ከተወለደ በኋላ፡ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው፡ በእምነት፡ ሦስት ወር ሸሸጉት፤ የንጉሥንም አዋጅ አልፈሩም።**
>
> **ሙሴ** ካደገ **በኋላ፡ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል፡ በእምነት እምቢ አለ፤**
>
> **ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ** ስለ **ክርሰቶስ መነቀፍ፡ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አሰቦአልና ለጊዜው በኃጢአት፤**
>
> **ከሚገኝ** ደስታ **ይልቅ፤**... **ከእግዚአብሔር ሕዝብ** ጋር **መከራ መቀበልን መረጠ** ብድራቱን **ትኩር** ብሎ **ተመልክቶአልና።**
>
> **የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ፡ የግብፅን አገር የተወ፤ በእምነት ነበር፡** የማይታየውን **እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና።**

34 ዛሬ ጠዋት፡ "በእምነት መምረጥ፡" በሚል ርዕስ ጉዳይ እናገራለሁ። መነሻ የሚሆነኝ ጽሑፍ፡ ከ23ተኛው ምዕራፍ **ሙሴ፡ በእምነት፡** የሚሉ ሶሰት የመጀመርያ ቃላት እጠቀማለሁ። "በእምነት መምረጥ፡" ሰንል፡ አብዛኛው የምናደርጋቸው ነገሮች፡ በእምነት ልንመርጣቸው ይገባናል። ሙሴ ያደረገው ሁሉ፡ አሁንም ቢደገም የሚገባው፡ በእምነት ነበር፡ በእምነት እንጂ፡ በማየት አልነበረምና።

35 ዛሬ ጠዋት ይሄን የመረጥኩበት ምክንያት፡ በዚህ ሁኔታ ላሉ ቤተ ክርስቲያን፡ እንዲሁም በእኛ ዘንድ... በየትምህርት ቤቶቻችን፡ በዙርያችን ሁሉ፡ ሳይንሳዊ ትምህርት በመብዛቱ ነው። በዚህም ምክንያት፡ ህዝብ ከእምነት እንዲርቅ አድርገነዋል። እምነት፡ በሳይንስ አይመረመርም። እምነት ሳይንስ የማያየው ነገር ነው። እኛም... ይህ ታላቅ እምነት ብንጥል፡ በድቅድቅ ጨለማ እንኖራለን፡ ምንም ያህል... የተማርን ብንሆን፡ ወይም ለእምነታችን እንደሚመች አድርገን፡ የእግዚአብሔርን ቃል መተንተን ብንችል።

36 በእምነት ካልሆነ በቀር፡ እግዚአብሄርን የምናስደስትበት ሌላ መንገድ የለም። ይሄኛው ቃል በግልጽ አስቀምጦታል፡ በእምነት ነው። "ያለ እምነት፡" ይላል ቅዱስ ቃል ሲናገር፦ "እግዚአብሄርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።"

37 ስለዚህ፡ እምነት ከሳይንስ ጋር፡ ሳይንስም ከእምነት ጋር መስማማት ከሌላቸው፡ እንዱ ለሌላው—ሁለቱ ጠላቶች ያደርጋቸዋል፡ ስለዚህ ሙሴ እንዳደረገው ምርጫችን መለየት አለብን። በእምነት እናምናለን!

38 ስለዚህ፡ እምነት ከሌለን፡ ከእግዚአብሄር የሚመለስ ጸሎት በፍጹም አይኖረንም። "ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ፡ እግዚአብሄር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።" ስለዚህ እምነት ካጣን፡ ጸሎታችን ተሸሮአል፡ የትም አንደርስም።

39 ስለዚህ የእኛ አሳብ፡ ዛሬ ጠዋት፡ እምነትን አጥብቆ ለመያዝ ነው። እንግዲህ፡ እምነት ከጠፋብን፡ ተስፋችን ሁሉ ይጨልማል። እምነት ከጠፋብን፡ መንፈሳዊ እውነታዎቻችን ይጨልማሉ። ምክንያቱ፡ በሚታይ ነገር እምነትን ማጽናት አትችሉም፡ የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ጠፊዎች ናቸውና።

40 አንድ ታላቅ ሰው፣ ታላቅ አገልጋይ፣ ወይም ታላቅ ጉባኤ ያየን እንደሆነ፣ አንድ ቀን፡ ሁሉም ይጠፋሉ። አንዲት ታላቅ አገር፣ ወይም ታላቅ የጦር መሣርያ ያየን ከሆነም፡ አንድ ቀን፡ ሁሉም ይጠፋሉ። ስለዚህ ሳይንስ ባላረጋገጣቸው ነገሮች፡ መኖር አለብን። የምናምነው በእምነት ነውና።

41 አሁን፡ እምነታችን ከጠፋ፡ ክብራችን ይጠፋል። ከእምነት ፈቀቅ ካልን፡ ቤተክርስትያንን፡ ወደ አእምሯዊ እውቀት እንዘውራታለን።

42 ብዙ ጊዜ፡ በሰዎች ዘንድ፡ የሚታሰበው፡ አንዲት ማሕበር እጅግ ግዙፍ ስለሆነች፣ ታላላቅ አብያተ ክርስትያናት፡ ታላላቅ ካቴድራሎች፡ ጌጠኛ-ልብስ የለበሱ፡ አንጋፋ ሰዎች፣ እና እነኚህን ለማድረግ የሚያስችላቸው፡ ብዙ ገንዘብ ስላላቸው ብቻ፡ ብዙ ጊዜ፡ ምሪት ያላቸው ይመስለናል፡ ይሄኛው ቤተክርስትያን ምሪት ተቀብሏል እንላለን። ወይም፡ አብዛኛው ጊዜ በየመስኩ ወጥተው ብዙ ሕዝብ የሚሰበስቡ አገልጋዮችን እንጠቅሳለን፡ አንዳንዴም፡ የምሪት ምልክቶች እነዚህ ናቸው፡ ብለን እናስባለን። እውነቱ ግን ይህ አይደለም። ይህ ሰውአዊ ምሪት ነው።

43 እውነተኛ ምሪት ግን፡ አንድም ይሁን፡ ወይም በጣት ይቆጠሩ። የእግዚአብሄርን ፈቃድ በመፈጸም የሚመጣ ነው። አያችሁ? ትልቅ ቤተ ክርስትያን ይሁን፡ ትንሽ ቤተ ክርስትያን፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። ታላቅም ሆነ አልሆነ፡ እንደበተ ርቱዕ ይሁን፡ ሀሁ'ን የማያውቅ ሰው፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። የሚወስነው በሚያመጣው የመልዕክት ይዘት ነው፡ በእግዚአብሄር ቃል በተመራ ምሪት፣ ወይም፡ በሰዎች አእምሯዊ ዕይታ በተመራ ምሪት?

44 አንዳንድ ሰዎች በአንደበተ ርቱዕ ተናጋሪ ምክንያት ሊነኩ ይችላሉ። ስለ ተነኩ ግን ትክክል ነው ማለት አይደለም። አንዳንዴም ሰውየው ሐሳቡን በትክክል ማስቀመጥ የሚችል እጅግ የሰለጠነ ስለሆነ ብቻ በምሪት ይነካሉ። ይህ ማለት ግን ከእግዚአብሔር ነው ማለት አይደልም። አያችሁ?

45 ምሪት የምንቀበልበት ብቸናው መንገድ፡ ዘወትር ከሚኖር፡ ዘለአለማዊው ከሆነው የተባረከ ከእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ይህም በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ነው። እኛም በእምነት እንቀበለዋለን።

46 እስኪ አሁን ሙሴን፡ እና ያሳለፈው ታላቅ ህይወት እናስብ። መለስ ብለን፡ ስላወላለዱ፡ እና እግዚአብሔር እንዴት እንደተጠነቀቀለት እናነባለን፡ ሙሴ ግን በህይወቱ አንድን ነገር መምረጥ ወደ ሚገባው ጊዜ ደርሶ እናየዋለን። በትክክል ካነበብን፡ የፎርኦን የልጁ ልጅ፡ እና አልጋ ወራሽ እንደነበረ እንገነዘባለን፡ ስለዚህ በግብጽ ፎርኦን የሚሆን ቀጣይ ሰው እሱ ነበር። ወደ ተጣያቂነት ዕድሜ እንደደረሰ፡ ዙርያውን ሲመለከት አንድ ነገር አስተዋለ፡ በጭቃው ጉድጓድ ውስጥ የሚሰሩ ባርያዎችን መኖራቸውን ተመለከተ። ፎርኦን ሲያያቸው የኖሩ ባርያዎች፡ አሁን ሙሴ ከቤተመንግስቱ መስኮቶች፡ አማትሮ አያቸው፡ በምልከታው ግን የተለየ የእይታ ልዩነት ነበረው።

47 እኔም ዛሬ ጠዋት፡ በዚህች እሳቤ ላይ፡ መስረት መጣል እፈልጋለሁ፡ የሰማይ አምላክም ይህን ነገር ወደየልቦቻችን ያድርስ። ሁሌም ልዩነት የሚፈጠረው፡ ነገሮችን በምታዩበት እይታ ነው።

48 ጆን ስፕሮል፡ የተባለው የወንድም ቦስዋርዝ አገልግሎት ፍሬ የሆነው፡ ታላቁ ወንጌላዊ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ ከኦልድ ግሎሪ ባርን የሆናችሁ ብዙዎቻችሁ ታስታውሱታላችሁ። ውድ ባለቤቱ እና ሚስቱ ከመሞቷ በፊት፡ አንድ ቀን ለጉብኝት፡ ወጣን አለ። ላ ሴላ፡ ሎሬን፡ ፈረንሳይ አገር፡ ነበር የሄዱት። እኔም ይህ ቦታ ለማየት ዕድል አግኝቼ አይቼዋለሁ። አስጎብኚው በጋርደኖቹ መካከል እየመራቸው፡ የተለያዩ ነገሮች ያሳያቸዋል። እና የጌታ ኢየሱስ፡ የስቅለት ሐውልት ጋር ደረሱ። አቶ/ ስፕሮል እና ሚስቱ፡ ቆመው፡ ሐውልቱን ተመለከቱት፡ እና፡ አርቲስቱ፡ ይህ ሐውልት ስሪ ይሄን ሲሰራ፡ ምን እያሰበ ነበር፡ በማለት በልባቸው ወቀሱት፡ ድንጋዩን ሲፈለፍል፡ እንዲህ አይነቱ አስቀያሚ-ገጽታ የጌታ ኢየሱስ ስቃይ እና ፍቅር እና መከራ ምሳሌ እንዴት ይወክላል፡ ደግሞም ጉርብጥብጥ ያለና ጥርበት-የበዛበት ይመስላል። አስጎብኚው ወደ አቶ/ ስፕሮል ቀረበና፡ "ጌታየ፡ ይሄን የጌታ ኢየሱስን ሐውልት እየተቸህ እንዳለህ እገምታለሁ፡" አለው።

እርሱም "አዎን፡" አለው።

49 እርሱም፡ "ብዙም አይገርመኝም፡ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያዩት፡ ይተቹታል፡" አለው።

50 እና አቶ/ ስፕሮል እንዲህ አለ፦ "እንዴት ነው፡ ምንም ዓይነት የሚያሳዝን እና የሚነካ ስሜት አላየሁበትም፡ ቀራጺው ለምን እንዲህ እንደ ሰራው አሳሰቦኛል።"

51 "ቀራጺውም... " እሱም እንዲህ አለው፦ "አቶ ስፕሮል፡ ሐውልቱ ችግር የለበትም፡ የቀራጺው ሐሳብም ትክክለኛ ነው። ችግሩ ያለው፡ አንተ ጋር ነው። አንተ የምታይበት ምልከታ ይወስነዋል።" እርሱን እና ሚስቱን በእጆቻቸው

ይዟቸው፡ ከመስቀሉ ስር ወዳለው መሰውያ ወሰዳቸው። "አቶ/ ሰፕሮል፡ አሁን፡ ወደ ላይ ተመልከት፡" አለው። ወደ ላይ በተመለከተ ጊዜም፡ ልቡ ልትክደው ደረሰች። በዚያ አቅጣጫ በኩል ቆመህ **ያንን** ማየት፡መታየት ባለበት መልኩ፡ እንዲታይ በተሰራበት በኩል ማየት፡ እንዴት ያለ ልዩነት ነው።

52 እምላክም እንዲህ ነው። እምነትም እንዲህ ነው። እንደየ እይታችን ነው። መጽሓፍ ቅዱስ ዘመኑ ያለፈበት፡ ታሪካዊ መጽሐፍ እንደሆነ አድርጋችሁ ከተመለከታችሁት፡ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ ጥቅም በፍጹም አታገኙትም። በጉልበታችሁ ተንበርክካችሁ፡ የዚህን መጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዛት መጠበቅ፡ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ አይን አልፋችሁ ማየት ይኖርባችኋል።

53 እስኪ በዚህ ማለዳ፡ ጉባኤውን ልጠይቅ። እግዚአብሄር ዛሬም ያው ካልሆነ ታሪካዊ እግዚአብሄር ምን ይጠቅመናል? ሙሴን ተጠቅሞ የሠራውን ተአምራት ያደረገ አምላክ፡ ዛሬም ያው ካልሆነ፡ እንዲህ አይነቱ አምላክ ማንበባችን ጥቅሙ ምንድነው፡ ምንስ ይሰራልናል? የዕብራውያን ልጆች ከእሳት እቶን ያዳነ አምላክ፡ ዛሬም ያው ካልሆነ፡ ምን ይጠቅመናል? ባለፈው ዘመን፡ በጻዲቁና በክፉ መካከል የሚፈርድ አምላክ፡ ዛሬም ያው አምላክ ካልሆነ፡ ክፉውን ቀጥቶ ጻድቁን መባረኩ ምን ይጠቅማል? ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዳችን ለምን አስፈለገን? እርሱ የሚፈርድ ያው፡ እና እንደ ጥንቱ አንድ ሐሳብ ያለው አምላክ ካልሆነ፡ ከዓለም ነገሮች መራቃችን ለምን አስፈለገ? በከባድ ትኩሳት የተያዘች ሴት እጇን በመዳሰሱ፡ ትኩሳቷ ቢለቅቃት፡ እርሱ ያው አምላክ ካልሆነ ምን ይጠቅማል? ለአራት ቀናት የሞተውን ወዳጁ፡ ከመቃብር እንዲወጣ ያደረገ አምላክ፡ ዛሬም ያው አምላክ ካልሆነ ምን ይጠቅማል?

54 እኛንም በታላቁ ቀን ከምድር እንደሚጠራን በእምነት እናምናለን፡ እንዲት ማንኪያ አመድ ሆነን ብንቀርም ይጠራናል። በምን እናረጋግጣለን? እናረጋግጥም። እናምናለን እንጂ። ሁሉንም ነገር እንድናምን እንጂ። እንድናረጋግጥ አልተጠራንም።

55 ሙሴ በእምነት **እንዲህ-እና-እንዲያ** አደረገ። ሙሴ፡ እንደ ወጣት ሰው፡ በቤተ መንግስቱ መስኮት በኩል፡ ባርያዎቹን አያቸው፡ ፎርኦን ሲያያቸው የኖሩትን የቦኩ፣ የቆሸሹ፣ ጭቃ-ተሸካሚ ባርያዎች ተመለከተ።

56 ፎርኦን እና ግብጻውያን፡ ሲመለከቷቸው፡ ትርጉም የሌላቸው የባርያ መንጋዎች ነበሩ። ከጭቃ አብኩነት የዘለለ፡ ለሌላ ነገር የማይጠቅሙ፡ ፎርኦን ለሚያስራቸው ከተሞች የጭቃ ጡብ ሰሪዎች ናቸው። በባርያዎቹ ላይ የግብጻውያን እና የፎርኦን እይታ ይህ ነበር።

57 ሙሴ ሲያያቸው ግን፡ የሙሴ እይታ፡ ይለይ ነበር። በመስኮት አልፎ፡ የፊታቸውን መጎርጎድ፡ በጉንጫቸው የሚወርደው እንባ፡ ሲያይ፣ የጎበጠው አካላቸው ተመልክቶ፡ እንደ እግዚአብሔር ህዝብ ተመለከታቸው። እንደ ተመረጠ የእግዚአብሔር ህዝብ እንጂ። እንደ ባርያዎች አላያቸውም።

58 ኦ፡ እኔም፡ ከአገር ወደ አገር፡ ከአንዱ ህዝብ ወደ ሌላ ህዝብ፡ እየተጓዝኩ በምሰበክበት፡ ወቅት! ይህች ትንሿ ጉባኤ ከእምነት ተቋማት ሁሉ የተውጣጣች፡ ከፍቅር በቀር ሌላ ሕግ የሌላት፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር፡ ሌላ መጽሐፍ የማታውቅ፡ ከክርስቶስ በቀር ሌላ ስርዓት የሌላት ትቼ ስሄድ፡ የእግዚአብሄር

ልጆች የሆኑትን፡ የተናቁትን ሁሉ፡ እንደ አምላክ ምርጦች እና እንደተመረጠ ህዝብ ለማየት ሞክሬአለሁ። የብራንሃም ተበርናክል አባል ናችሁ ወይ አልላቸውም። ሜቶዲስት ናችሁ፡ ወይም ፕሪስባይቴሪያን ናችሁ፡ አልላቸውም ጴንጤዎች ናችሁ፡ ናዝሪኖች ናችሁ፡ ወይም ፕሊግሪም ሆሊነስ ናችሁ ብየ አልጠይቅም። እንደ እግዚአብሔር ህዝብ እንድመለከታቸው እፈልጋለሁ። የጌታ የእግዚአብሔር ባርያዎች መሆናቸው፡ የሚያደርጉት ስራዎች አያለሁ። ምንም ዓይነት ብራንድ ይኑራቸው፡ ልቤ ከእነርሱ ጋር ሕብረት ማድረግ ይናፍቃል። ሕብረታቸው ይናፍቀኛል። የእግዚአብሔር ህዝብ መሆናቸውን ስለማውቅ፡ እወዳቸዋለሁ።

59 ረጅም ቀሚስ የለበሰች፡ ጸጉሯም በስርዓት ወደ ኋላዋ የወረደ ሴት፡ መንገድ ላይ ስትመጣ ባይ፡ አለባበሷም-ልከኛ ልብስ—ቢሆን፡ ሌላም ምናልባት ተመሳሳይ ዕድሜ ያላት፡ አጭር ቁምጣ የለበሰች፡ ሌላ ወጣት እመቤት ባይ፡ ምናልባት እንደ ዓለም እይታ፡ ከባለ ረዥም ጸጉሯ፡ በእጥፍ፡ የምታምር ልትሆን ትችላለች፡ እኔ ግን እንደ ክርስትያን ከለበሰች ሴት ጋር እደግፋለሁ። ምንም ያህል ወግ አጥባቂ ነሽ ቢሏት፡ ቢሳለቁባትም፡ እኔ ግን፡ እደግፋታለሁ። እንደ ሌላኛዋ ሴት፡ ለተመልካች የማትማርክ ልትሆን ትችላለች፡ ነገር ግን የሆነ ነገር እይታለች። በእምነት የማይታየውን፣ ህይወቷን የሚመራውን እይታዋለች።

60 አንድ ሰው በሰራ ቦታው፡- "ዲያቆኑ፡" ወይም "ሰባኪው፡" ወይም "ወግ አጥባቂው" ሲባል፡ አላጨሰም ስላለ፣ ቢራ አልጠጣም፣ እንደሌሎቹ፡ ጭፈራ አልጨፍርም ሰላለ፡ "ወግ አጥባቂው" ሲሉት፡ ልቤ ይራራለታል። በግብጽ ምድር ሆነን፡ ልባችን ለመተቃቀፍ እና እንዲህ ለመባባል የምናፍቀው፡ ወንድሜ ነው፡- "ወንድሜ፡ እኛ በምድር ሰደተኞች እና መጻተኞች ነን፡ ከአንተ ጋር ህብረት ማድረግ ይናፍቀኛል።"

ሙሴ የእምነት ምርጫ፡ መምረጥ ነበረበት።

61 የፎርኦን ሴት ልጅ ልጅ ለመባል'ማ ስንት እና ስንት ሰዎች ተራግጠውበታል! የሙሴን ዕድል ቢያገኙ ስንት እና ስንት ወጣቶች ዘለው በገቡ ነበር፡ በዓለም ከሚገኘውን ደስታ እና ፈንጠዝያ ለመደሰት፣ የግብጽ ንጉስ ልጅ ለመባል፣ ዓለምን እና መላዋን ከእግርህ ስር ለማድረግ! "እንዴት ያለ ሞኝነት ነው፡" በዘመኑ የነበሩት ወጣቶች እንዲህ እሰበው ይሆናል፡- "ሙሴ ዕጣፈንታውን ከተጎዳው እና ከተመታው የእግዚአብሔር ህዝብ አደረገ።"

62 ለምን እንዲህ ያደርጋል? ብለዋል፡ በእምነት ዓይኑን ባነሣ ጊዜ ግን፡ ከዓለም ውበት ባሻገር አየ። ከኃጢአት ደስታ ባሻገር አየ። መጽሐፍ ሲናገር የማይታየውን እንደሚያየው፡ በእምነት ሰለቆጠረ፡ ምንም ይሁን ምን እግዚአብሄርን ለማገልገል ምርጫው አደረገ።

63 አሁንም አልተለወጠም። ብዙዎቻችን'ኮ የተሻለ ወደምንለው ሕንፃ መሄድ እንችላለን። ምናልባትም፡ በተሻለ ወንበር እና በተሻለ ጉባኤ፡ ልንደሰት እንችላለን። በማጨሳችን እና በመጠጥ፣ እንደ ዓለም አለባበስ በመልበስ፡ ታዋቂ ልንሆን እንችላለን። ታዲያ ምንድነው? አይናቸችሁን አንስታችሁ፡ የማይታየውን በእምነት እይታችኋልና፡ በዘመኑ-ከተጠሉት ጋር እና ሆሊ-

ሮለር ከተባሉት ጋር ለመጽናት አቋም ወሰዳችኋል። የማይታየውን በእምነት እናየዋለንና፡ ስቃይ እና መከራውን ለመካፈል እንመርጣለን።

64 ሰዎች መሰቃየትን መምረጥ እንዳለባቸው አልነግራቸውም። መከራን ምረጡ አልልም። ይሄን ማድረግ ሰብአዊነት አይሆንም። መከራ በግዴታችን ዕጣ ላይ ቢወድቅ ግን፡ በጸጋ እንቀበለው። ሰዎች እንዲያፌዙባችሁ እንዲህ አድርጉ አልላችሁም። ልዩ ነገር እንድትናገሩ አልፈልጋችሁም፡ “እኔ... **እንዲህ-እና-እንዲህ፡** በዓለማዊ ነገሮች፡ የማታምን ቤተክርስትያን አባል ነኝ፡” ወዘተረፈ የመሳሰሉ፡ ሰዎች ሊያፌዙባችሁ የሚያደርጋቸው ነገሮች አልፈልግም። እራሳችሁ ናችሁ የምትጎትቷቸው። እዚህ ወጥታችሁ እንዲህ አድርጉ የአክራሪያን ነገር አድርጉ አልልም። ወግ አጥባቂያን ናችሁ እንዲሏችሁ ብየ፡ ይሄን አድርጉ ለማለት አልፈልግም። በላያችሁ የምትጎትቱት እራሳችሁ ናችሁ። የእግዚአብሔር ግዴታ ዕጣ ፈንታህ ላይ ከመጣ ግን፡ ዓለም ማለት የሚፈልጉትን ይበሉ። አንተ ትኖራለህ።

ምርጫህን አድርግ። ሴትም ወንድም ሁሉ ምርጫው ይመርጣል።

65 ሙሴ ያየውን ነገር ፎርኦን ማየት ቢችል ኖሮስ? እሱ የህዝቡን ስቃይ ተመልከተ። የሚከፍለው ዋጋ ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር። የኃጢአትን ደስታ ከማግኘቱ ይልቅ ግን በእምነት እሱን መረጠ።

66 ምናልባት አሁን እናንተ ሴቶች፡ እጅግ የምታማምሩ ወጣት ሴቶች፡ እዚህ ልትኖሩ ትችላላችሁ። ዓለም እንዲህ ሊልሽ ይችላል፦ “**እንዲህ-እና-እንዲያ** አድርጊ። አንቺ’ኮ ቆንጆ ነሽ። ቅርጽሽ ልዩ ነው። ተጠቀሚበት እንጂ።”

67 አንቺ ግን፡ እህቴ ሆይ፡ አይኖችሽን አንሺና የተናገረውን አሰቢ፡ “ሴት የወንድ ልብሰን ብትለብሰ ነውር ነው፡” ብሎ የተናገረውን ተመልከቺ።

68 የሰፈር ወንዶች ልጆች፡ ወይም ሴቶች ጓደኞቻችሁ፡ እንዲህ ብሏችሁ፦ “ረጅሙን ጸጉርሽ ቁረጪው። የሚያምር ይሆንልሻል። **እንዲህ፡ እንዲያ፡** ወይም **ልዩ** ይሆናል።” ወይም፡ “ቆንጆ ትሆኛለሽ።” በፍጹም ጆሮ አትሰጪ!

69 በእምነት አይኖችሽን አንሺ፡ እርሱ የተናገረውን አሰቢ፦ “የሴት ልጅ ጸጉሯ ክብሯ ነው፡ ጸጉሯ አይቆረጥ ብሏል።”

70 እንዲህ፦ “ታዋቂ ትሆኛለሽ ቢሉሽ። ወይም ከአለቃሽ ጋር፡ የወዳጅነት መጠጥ ብትጠጪ፡ በሰራሽ ላቅ ወዳለ ደረጃ ትደርሻለሽ። እንደ ሌሎቹ ሴቶች ሲጃራ ብታጨሺ፡ በሰፈር በመንደር የተሻለ ተቀባይነት ይኖርሻል ቢሉሽ።”

71 በእምነት አይኖችሽን አንስተሽ “ይህን አካል ብታቆሽሹት፡ እኔ አጠፋዋለሁ፡” ያለውን ተመልከቺ። በእምነት እነዚህን ነገሮች እናምናለን። የምታምኑት እንጂ። የምታዩት ነገር አይደለም። ሙሴ፡ በእምነት አደረገ።

72 ስለዚህ በዚህ የእምነት ጉዞ፡ የምርጫ ጉዳይ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል።

73 ሎጥ እንደኛ ዓይነት መጥፎ ምርጫ መረጠ። ብዙ ጊዜ ሰለ ጥቅማችን ብቻ እንመርጣለንና። የተሻሉ የምንላቸውን ነገሮች እንመርጣለን።

74 አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትንሽ ሽኩቻ ሲነሳ፣ አንዱ ተነስቶ “ዲያቆኑ፡ ወይም ፓስተር ከዚህ ጎራ ናቸው፡” ይላችኋል። ከጽድቅ የሆነውን ተመልከቱ እንጂ። እንዲህ አይነቱን አትመልከቱ። ያንን ነገር አውጥታችሁ ፊት ለፊት አቀራርቧቸው። አምላካዊ ማለት ይህ ነው።

75 ምርጫ አለ። እኛ ስንመረጥም ለራሳችን ነው። ለእኛ ሁላችንም የሚበጀኝ ምርጫ እንመርጣለን።

76 ሙሴ ግን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ይሄድ ዘንድ፡ መከራውንና ውርደትን መረጠ። አሁን አስቡት። አዳምጡት። “የእግዚአብሔርን ሕዝብ መከራ መረጠ፡ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን ስላሰበ፡ የማይታየውን፡ እንደሚያየው አድርጎ ጸና።”

አሁን፡ አንድ ጊዜ፡ ሎጥ፡ መምረጥ ግድ ሆነበት።

77 እና ምናልባት፡ ዛሬ ጠዋት፡ እዚህ ከተቀመጣችሁ ወንዶች እና ሴቶች፡ የመጨረሻ ምርጫችሁ የምታደርጉ ልትኖሩ ትችላላችሁ። እናንተ ዛሬ የሆናችሁት ነገር ለመሆን፡ ከብዙ አመታት በፊት አሁን የሆናችሁትን ለመሆን ስለመረጣችሁ ነው። አሁን የምትመርጡት ምርጫም የዛሬ አምስት አመት ምን እንደምትሆኑ ይወስናል። ከአምስት አመት በኋላ ሚሽነሪ ልትሆን ትችላለህ። ከአምስት አመት በኋላ ታዋቂ ክርስቲያን ልትሆኑ ትችላላችሁ።

78 ወይም፡ በተሳሳተ ምርጫችሁ ምክንያት፡ የዛሬ አምስት አመት ገሃነም ልትገቢ ትችያለሽ። የዛሬ አምስት አመት ባር ውስጥ ፖፖ አጣቢ ልትሆኚ ትችያለሽ። የዛሬ አምስት አመት ጎዳና ላይ ሴተኛ አዳሪ ልትሆኚ ትችያለሽ።

79 ወይም፡ ክርስቶስ በመምረጣችሁ፡ ሴትም ይሁን ወንድ—በማሕበረሰብ ውስጥ ክብር ልትሆኑ ትችላላችሁ። ዛሬ ባደረጋችሁት ምርጫ ምክንያት፡ የዛሬ አምስት አመት ወደ ክብር ልትወሰዱ፡ ልትነጠቁ ትችላላችሁ።

80 መምረጥ ግን አለባችሁ። ስትመርጡ የሚታየውን አትመልከቱ። በእምነት የሚታይ ምረጡ። ተቀባይነት ያለው ብቸኛ ነገር፡ በእምነት የምትመርጡት ነው።

81 ሎጥ፡ ምርጫውን ስለመረጠ። ሎጥ የመረጠውን አብራሃም ሰጠው።

82 እግዚአብሔርም ምርጫችሁን ይሰጣችኋል። “የምታገለግሉትን ዛሬ ምረጡ።” በኤደን ገነት ውስጥ—የእውቀት ዛፍ፡ እና የሕይወት ዛፍ ነበሩ። የሰው ልጅ የሚፈልገውን አንዱን እንዲመርጥ እድል ተሰጠው። ዛሬም እንዲሁ ነው። ነጻ ስነ ምግባራዊ ውክልና እንዳላቸው፡ የምትፈልጉትን ምርጫ፡ የመምረጥ መብት ተሰጥቷችኋል።

83 እኔ ዛሬ ለእናንተ የምመክራችሁ፡ በዙሪያ ያሉትን ዘመናዊ ነገሮች፡ እና እናንተ የምትሆኑትን አንጋፋነት እና ማራኪነትን አትመልከቱ። ይልቁንስ፡ በእምነት፡ አንድ ቀን መጥቼ የተበላሸውን ነገር ሁሉ እቃናለሁ፡ ከፍ አደርጋችኋለሁ፡ የዘለአለም ህይወት እሰጣችኋለሁ በማለት፡ ቃል የገባውን ምረጡ። የጌታ ከሆኑት ጥቂቶች ጋር የተናቀውን መንገድ ብትመርጡም፣ ምርጫችሁ አድርጉት። እጃችሁ ላይ ችግር ቢኖር፣ ምድሪቱ ላይ ችግር ቢኖር፣ ቤተክርስትያን ላይ ችግር ቢኖር፣ በቤት ውስጥ ችግር ቢኖር፣ ችግር የትም ቢኖር፡ ምርጫችሁን ፈጽሙ፦ “በእምነት እግዚአብሔርን አገለግላለሁ። በፊቱ ልቤን አዋርዳለሁ። ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር መንገዴን አደርጋለሁ። ሲናቁ እና ሲጣሉ፣ አባርረው ሲሳለቁባቸው ባይ፣ አሁንም ግን በመጠበቅያዬ እጸናለሁ። እዚያው እጸናለሁ። ሲያለቅሱም፡ አብሬያቸው አለቅሳለሁ። ኃዘንም በሆን ጊዜ፡ ከእነርሱ ጋር አዝናለሁ። እንደ አኗኗራቸው፡ እኔም እኖራለሁ።”

84 ኑኃሚን... ወይም ሩት ኑኃሚንን እንደተናገረቻት፡ “መንገድሽ መንገዴ። መንገዴም መንገድሽ ይሁን። በምትኖሪበት፡ እኖራለሁ። ወደ ምትሄጂበት ሁሉ፡ እሄዳለሁ። አምላክሽ አምላኬ ይሆናል።” ምንም እንኳን እከሌ ነኝ የምትሉበት፡ የህሊና ቆዳችሁን የሚገፍ ቢሆንም፡ እሱን ምረጡት። ቆዳችሁን ግፈፉና አካሄዳችሁን የጌታ ከሆኑት ጥቂቶች ጋር አድርጉ፡ በመጠበቅያችሁ እና በአገልግሎታችሁ ታማኞች ሆናችሁ ቆዩ።

85 ሎጥ ዙርያውን አይቶ፦ “የምመርጠውን አገኘው።” አለ። ወደ ሶደም ተመልክቶ። አብራሃም ይኖርበት ከነበረው፡ የሚበልጥ መልካም የግጦሽ ሳር ያለበትን ምድር አየ። እንስሶቹን የሚያበላበት፡ የተሻሉና ወፋፍራም ከብቶች እንዲኖሩት የሚያስችለው ዕድል አየ።

86 የማንንም ስሜት እንደማልጎዳ ተስፋ አደርጋለሁ። ይሁን እንጂ የብዙዎች ሰባኪዎች አቋም ይህ ነው፡ ብዙ ገንዘብ አገኛበታለሁ፡ ብለው በማሰብ ወንጌል ላይ ያመቻምቻሉ። ለደመወዝ ሲሉ! በእግዚአብሔር ቃል ያለኝን የእምነቴን ትምክህት ላይ ከማመቻምች፡ ከምንጭ ውኋን፡ እየጠጣሁና፡ እየበላሁ፡ ደረቅ ቂጣ እየተመገብኩ ባዶ ምድር ላይ ብኖር ይሻለኛል። አቋሜን አጸናለሁ።

87 አንዳንዶች ሲናገሩኝ “ቢሊ ግን፡ ጉባኤዎችህ ምንድናቸው፡ ጴንጤቆስጣሎች ይበዙበታል፡” ይሉኛል። ይህን የተናገረው አንድ ታላቅ የድርጅት አገልጋይ ነው።

እኔም አልኩት፦ “ድርጅታችሁ ጉባኤዬን ስፖንሰር ያደርግልኛል ወይ? ”

88 በቅርብ ጊዜ ነው፡ **ሉክ** በተባለው ጋዜጣ ይመስለኛል፡ አንድ አንቀጽ ወጥቶ ነበር። ጸሐፊው በዚያ የተናገረው፡ ስለ ጴንጤቆስጤ ህዝብ ነበር። “የጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያን በዓለም ካሉ እምነቶች ሁሉ ፈጣን እድገት እያስመዘገበ ይገኛል፡” በማለት ይገልጻል። ለምን ሲባል? ወንዶች እና ሴቶች አይኖቻቸውን አንስተው አርቀው ሰላዩ ነው።

89 ጸሐፊው በተጨማሪ የጴንጤቆስጤን ህዝብ አደናንቋል። በርግጥ፡ አዎን፡ እሱ፦ “ጽንፈኞች፡ እና የመሳሰሉ ነገሮች እንዳሉ ተናግሯል። ሜተዲስቶች በቤተ ክርስትያን መመርያ ያመልካሉ። እግዚአብሄርን በቤተ ክርስትያን መመርያ ያመልኩታል። ባፕቲስቶች፣ እና ፕረስቢተርያኖችም ያው ናቸው። ጴንጤቆስጣሎች ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ያመልኩታል ብሏል።”

90 የተስፋውን ቃል በእምነት እናያለን። ዕጣዬን ከእነርሱ ጋር አደርጋለሁ፡ ምንም ያህል የተናቁ ቢሆኑም፡ አሁንም ከእነሱ አንዱ ነኝ። ምንም እንኳን መሳለቂያ ቢሆኑ፡ እንደ እስራኤል ውጣ- ውረድ-ቢበዛባቸውም፡ ከበልዓም፡ ከሐሰተኛው ነብዩ ጋር፡ በተራራው ላይ በፍጹም አልቆምም፡ እግዚአብሔር የባረከው ፈጽሜ አልረግምም። ምክንያቱም በዚያ ሰፈር ውስጥ፡ የተመታ ዓለት፡ እና ደም የተሞላ መሰዋዕት፡ እና የእሳት ዓምድ አለ። ምንም ነገር ውስጥ ቢገቡም፡ ወደ ድል እየመራቻው ነው፡ ወደዚያም መድረሳቸው አይቀርም፡ በእምነት የሚጓዙ የተስፋ ቃል ህዝብ ናቸውና። የእምነት ተቋም ባይሆኑም፡ በየሰፍራው የሚቅበዘበዙ ሲሆኑ፡ የእግዚአብሔር ህዝብ ናቸው። እኔ ግን አካሄዴ ከእነርሱ ጋር በማድረግ፡ በመጠርያቸው አብሬ ብሆን እመርጣለሁ። በእምነት ተቋማቸው ውስጥ ሳይሆን፡ በእግዚአብሔር በዘለአለማዊ መንፈስ አንቀጾች ውስጥ ባለው ህብረት፡ በእርሱም፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በእምነት

ተቀብያለሁ። ሁሌም እንደዚህ አይነት አመለካከት እንድይዝ እግዚአብሔር ይርዳኝ።

91 አስታውሱ። እየተጓዙ ሳሉ፡ ሎጥ ከብቶቹን የሚያ—ወፍርበት ዕድል ማየቱን ተመልክተናል። ብዙዎች ኪስ የሚያወፍርላቸው ዕድል አዩ። ብዙዎች በማሕበረሰብ ተቀባይነት የሚያገኙበትን ዕድል አይተዋል። ተጨማሪ ጥቂት ዶላሮችን የሚያስገኝለት አጋጣሚ አየ። የከተማይቱ ከንቲባ የሚሆንበት አጋጣሚ አየ። እንግዳ ከመሆኑ፡ እና ብልጣ ብልጥ፡ እንደመሆኑ መጠን፡ "ምናልባት የከተማይቱን አለቃ ልሆን እችላለሁ።" በፊቱ ተዘርግተውለት ነበሩና አጋጣሚዎቹን አያቸው። ምድሪቱን ሊያነድድ ያለው እሳት ግን አላየም ነበር። ምድሪቱ በሐጥያት ተሞላታ፡ እግዚአብሄርም ሊያጠፋት እንዳለ አይቶ፡ ከራሱ ጋር አልታረቀም።

92 ዛሬም፡ ሰዎች፡ "አንተ... እንዲህ ነው? " በማለት ከራሳቸው ጋር መታረቅ ይጥራሉ፡

"ክርስትያን ነህ ነሽ? " ስትሏቸው፡

93 "አሜሪካዊ ነኝ፡" ይላሉ። ቊራን አንተ እንቊራሪት ነህ እንደ ማለት የዘለለ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም።

94 እግዚአብሄር ጻዲቅ ነው፡ መጥፋቷ አይቀርም። አሜሪካን ከሐጥያቷ ጋር ከተዋት'ማ፡ ቅዱስ የሆነው ጻድቅ እና ልዑል አምላክ፡ ሶዶምን እና ጎሞራን—የማስነሣት ግዴታ ይኖርበታል እኛን እንዲሁ ከተወን፡ በሐጥያታቸው ምክንያት ስላቃጠላቸው፡ ይቅርታ ሊጠይቃቸው በተገባው።

95 እስከነ ክፉ ስራዎቻችሁ ወደ ገነት ካስገባችሁ፡ አናንያስን እና ስጲራን ቀስቅሶ ሌላ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባዋል። ማድረግ ይገባዋል። እርሱ ግን ጻድቅ ነው። አናንያ ገንዘቡን አየ። ጴጥሮስ ክርስቶስን አየ።

96 ኦህ፡ ማይ! ሎጥ በዚያ አገር የልጆቹን መጥፋት አልተመለከተም።

97 ዛሬ ዛሬ፡ ተራ የሆነውን የእምነት ስርዓት እና ወዘተ የያዛችሁ፡ ብዙዎቻችሁ፡ ልጆቻችሁ በወጣት ዕድሜአቸው የሚፈጽሙት ወንጀል እና መጥፋታቸው አታስቡም። ሴት ልጃችሁ በሴተኛ አዳሪ ቤት ውስጥ አታስቧትም። ወንድ ልጃችሁ መጠጥ ቤት ውስጥ፡ ወይም ቁማር ቤት ውስጥ አታስቡትም።

98 ሐጥያት ያልነካት። "ውኃ-ጠገብ ናትና።" የማህበረሰብ ሰብሳቢ ራስ የሆነው፡ እርሱ እያየ፡ ሚስቱ የጨው ዓምድ ስትቀየር፡ አላያትም። ህይወቱን ለማትረፍ፡ ወደ ትንሽ ከተማ በጥርሱ ጠርዝ ብቻ ሲያመልጥ፡ አላያትም። ይሄን አላየም፡ ምክንያቱ በፊቱ ያለውን ብቻ ይመለከት ነበርና።

99 አብራሃም ግን፡ ውኃ-ጠገብ የሆነውን፡ ምድር አልተመለከተም፡ አይኖቹን አንስቶ ነገውን ተመለከተ፡ የሁሉ ወራሽ እንደሚሆን አሰቧልና። እውነተኛው ክርስቲያን ዛሬም ዓይኖቹን አንሥቶ የክርስቶስን ተስፋ ያያል፦ "ትሑታን ብጹአን ናቸው ሁሉ ይወርሳሉና። ምድርን ይወርሳሉና።" እውነተኛው ክርስቲያን፡ በእምነት፡ ቀና ብሎ ይሄን ያያል። የፈለገ ነገር ብትሉት። አይኖቹን አሻግሮ ያያል። እርሱ እንዲህ ባደረገ ግዜም፡ እግዚአብሔር አብራሃምን "ምድሪቱ የአንተ ናትና፡ ተመላለስባት፡" አለው። አብራሃምም፡ በሙሴ እንደነበረች እምነት፡ በእምነት፡ እንዲሁ አደረገ።

100 አንዱ ተናጋሪ፡ የተናገረው ነገር አለ። በጣም ድንቅ ቃላት እንደሆኑ አሰባለሁ። አብራሃም-… “ሙሴ የዓለምን ዋና ነገር ወሰዶ በሚዛን በአንዱ ላይ አኖረው፤ እንዲሁም እጅግ የተናቀውን ሐይማኖት ወሰዶ፡ በሌላኛው ሚዛን አኖረው፤ የተናቀው ሐይማኖት ተመዝኖ-ከዓለም ዋና ነገር ይልቅ በለጠ።”

101 ዛሬም እንዲሁ ነው፣ መጥራት የፈለጉትን ነገር ቢጠሩን፡ “አክራሪ፡” ወይም “መለኮታዊ ፈዋሾች፡” ወይም “ሆሊ-ሮለርስ፡” ወይም የወደዱትን ነገር ቢጠሩን። የተናቀው ነገራችን ዓለም የተሻለ ብላ ከምታቀርበው ይልቅ-ይመዝናል። “ዘመኑ-ያለፈበት፣ ያረጀ ያፈጀ፣ አክራሪ፡” ብለው ሲጠሯችሁ ባትወዱም። ዲያብሎስ የተሻለ ብሎ ከሚያቀርብላችሁ ነገር ሁሉ ይልቅ-ይመዝናል። እርግጠኛ ሆኜ ይበልጠዋል።

102 ሙሴ ክርስቶስን አሰቀድሞ አይቶ። የክርስቶስን ነቀፋ እንደሚሻል ቆጠረ። በኋላም ስለ እርሱ ታላቅና አነቃቂ ቃላትን ተናገረ። “እነሆ፡ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል።” ያውቅ ነበር። እርሱን አሰቀድሞ አይቷልና፣ ከዓለም ውበት ይልቅ ከእርሱ ጋር መሰደብን የበለጠ ባለጠግነት እንደሆነ ቈጠረው።

103 ክርስቲያን ወዳጆች ሆይ፡ ዛሬስ፡ ይህን ማድረግ ያቅታችኋልን? የአለም ውበት እና ተወዳጅነቷ እያለ፡ በእምነት፡ ተሰፋ የሰጠንን እናየዋለን፡፡ እና ዛሬ በብዙ ነገሯ፡ እጅግ የተናቀች ቤተ ክርስትያን፡ ዲያቢሎስ ከሚያቀርባቸው ነገሮች ሁሉ ይልቅ-ትመዝናለች። በእምነት ተቋሞች እና በአክራሪነት፡ ብንስነጣጠቅም፡ ትንንሽ ሆነን ብንከፋፈል፣ ብንደናገርና ብንከፋፈልም፣ ዲያቢሎስ ከሚያቀርብላችሁ ነገሮች ሁሉ ይልቅ-ይመዝናል። በትክክል።

104 ከግብጽ ሀብት ይልቅ ከክርስቶስ ጋር መሰደብ እንደ ባለጠግነት ቆጠረ። ከዚያ በኋላ አንዳች ነገር ማድረግ ነበረበት። ግብጽን ትቶ ወጣ። አቤት፡ ይህን ቃል ሰወደው። ግብጽን ተወ። እነሆ፡ እርሱ ፎርኦን በሚያይበት ያው መሰኰት ተመለከታቸው፡ አሰተያየቱ ግን ተለየ። ፈርዖን ፍጻሜውን አይቶ ቢሆንስ? ፈርኦን ህዝቡ ሲሰጥም ቢያይስ? ሙሴ ግን አይቷል። እንዴት አየ? በሳይንስ ነው? ሙሴ፡ በእምነት አየ። እግዚአብሔር፡ ለአባቱ ለአብርሃም፡ ከአራት መቶ አመታት በኋላ፡ እንደሚጎበኛቸው ህዝቡንም ነጻ—እንደሚያወጣቸው ተሰፋ ስለ ሰጠ፡ ያደረገው ሁሉ በእምነት ነበር። ሙሴም እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል፡ በእምነት አመነ፡ ህዝቡን ነጻ ለማውጣት የተመረጠ መሪ መሆኑንም፡ በእምነት፡ እራሱን አወቀ። የነበረበትን ያውቅ ነበር። በጉድጓድ ውሰጥ፡ ጭቃ አብኩ ለመሆን ዕጣውን አነሳ፡ በግብጽ ዙፋን ከመቀመጥ ይልቅ ከክርስቶስ ጋር መሰደብ እንደ ታላቅ ባለጠግነት ቆጠረ። ወሰነ… በፍጹም “ሰለ እነሱ ሐዘን ይሰማኛል፡” ብቻ አላለም። ዕጣቸውን ተካፈለ እና አብሯቸው ሄደ። ክብር ይሁን… ዕጣቸውን ተካፈለ። እኛም አብረናቸው ሄደናል።

105 ምሪት የተቀበለውን ጸሐፊ እንዲህ ማለቱ አያሰገርምም፤

> አካሄደ ሰለ ጌታ ከተናቁ ጥቂቶች ጋር አደርጋለሁ።
> እቀጥላለሁ አሁን፡ ከኢየሱስ ጋር እጓዛለሁ።
> ወደ ከንአን ምድር መንገድ ጀምሬአለሁ። (አዎን።)

106 ሙሴ። አንዱ ሰለ ሙሴ ሲናገር፡ የፎርኦን ልጅ ተብሎ በዓለም ውበት መደሰት እየቻለ፡ የፎርኦን ልጅ ከመባል ይልቅ የአብራሃም ልጅ ለመባል

መረጠ አለ። የፎርኦን፡ የንጉስ ልጅ ከመባል ይልቅ፣ የተናቀው፡ የአብራሃም ልጅ መባል መረጠ።

107 የታላቋ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፕረሲደንት፡ ወይ ኤልቪስ ፕረስሊ ከመሆን፡ ወይም ፓት ቡን ወይም መሆን የምትፈልጉት ከመሆን፡ የጌታ የኢየሱስ እና አብሮ ከሚያገለግሉ ጋር ልጅ ብሆን፡ እና በዚህ ዓለም ከተናቀ ህዝብ ጋር፡ ዕጣ ፈንታየን ባደርግ፡ ይሻለኛል። ዕጣየን እነሣለሁ።

108 ወጣት ሴቶች ሆይ ዕጣችሁን እንሡ። ሜሪ ፒክፎርድን—ወይም፡ ታላላቅ የፊልም ስታሮችን፡ አንዳንድ ማራኪ ልጃገረዶችን ከመምሰል ይልቅ፣ ዕጣችሁን በጌታ ከተናቁ ጥቂቶች ጋር አድርጉ።

109 የሆሊውድ የፊልም ስታር፡ ወይም የምድር ታላቅ ሰው ከመባል ይልቅ፡ ፑልፒት ላይ ወጥቼ፡ የማይመረመረውን የክርስቶስ ባለጠግነት ብሰብክ ይሻለኛል። ትንሽ መብላት ካለብኝ፡ መለመን፡ ወይም ማድረግ ያለብኝን ምንም ቢኖር፡ ዕጣዬን ከጌታ ህዝብ ጋር አደርጋለሁ። በእምነት፡ አደርገዋለሁ። ብዙ ዕድሎች ቀርበውልኝ ያውቃሉ። በእግዚአብሄር ጸጋ ግን፡ አሁንም፡ በእምነት እያለሁ።

በእምነት ሩቅ ማየት ችያለሁ፡
አባታችንም መንገድ ላይ ይጠብቀናል፡
የምንኖርበት ስፍራ በዚያ ሊያበጅልን።

110 በቀደምለት፡ አንድ የቀረጥ ሰው፡ "ቤትህን ለምን ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን አዞርከው? የሀያ-አምስት-ሺህ-ዶላር የሚክል ቤት በዚህች ውበት-አልባ ቤተክርስትያን እንድትሰጥ ያደረገህ ምንድነው? አለኝ"

111 እኔም "ቤተክርስትያኒቷን አይደለም የሰራኋት። በውስጧ ያለውን ህዝብ እንጂ፡" አልኩት። በዓለም ውስጥ ከሚገኝ ነዋይ አንዳች የለኝም። የማገኛት ሳንቲም ሁሉ ወደዚህች ቤተ ክርስትያን ገብታለች። ለምን? እምነቴ በእግዚአብሔር እንጂ፡ በዓለም ባሉት ነገሮች ስላልሆነ ነው። ፍቅሬ ሰማያዊ ነው። እናንተም ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ከሆናችሁ፡ ያው እንደሆናችሁ አምናለሁ። እውነት ነው፡ እናንተም ናችሁ። እኛ፡ በእምነት፡ እንቀበላለን። በእምነት፡ ጌታን፡ እናምናለን።

112 ሙሴ፡ መምረጥ ነበረበት። ከዚያ በኋላ፡ ከመረጠ በኋላም፡ የንጉሱን ቁጣ አልፈራምና፡ እምነትን፡ መጋደል ነበረበት። አሁን'ኮ፡ እንደ ሰው፡ ቁጣውን የመፍራት መብት ነበረው። የንጉሱን ቁጣ የመፍራት መብት ነበረው፡ እሱ ግን አልፈራም። የሚሰራው ሰራ ስለነበረው፡ እና ግዴታውን በመወጣት ላይ ስለነበረ፡ አልፈራም። ንጉሱ ስለ ተናገረው ነገር ግድ አልሰጠውም። መንገዱንም እንዲሁ አደረገ።

113 አሁን፡ ፈርዖን፡ በእርግጥ፡ እንደተሸነፈ ሲመለከት፡ ሙሴንና ልጆቹን ሊሰጥ ፈልጎ ነበር… "ደህና፡ እኔ የማደርገው እነግራችኋለሁ። ሁላችሁም በምድሪቱ ትቆያላችሁ ወጥታችሁም ለአምላካችሁ መስዋዕትን ሠዉ፡" አለ።

114 ዲያቢሎስ የሚሠራው በዚህ መንገድ ነው። "ኦህ፡ ሃይማኖተኛ መሆን ትችላለህ። ሄደህ ቤተ ክርስቲያን ለምን አትቀላቀልም? እነዚህን ሁሉ ነገሮች ማድረግ አይጠበቅብህም።" አንድ ሰው ለሚስቱ እንዲህ አላት…

115 ሚስት እንዲህ አለች፦ "ባሌ፡ እኔ ድኛለሁ። ከአሁን በኋላ ማኒኩር፣ ወይም ሊፕስቲክ እና ነገሮች አልጠቀምም። ከአሁን በኋላ አልጠቀምም። ከአሁን በኋላ ባህላዊ ነገሮች ላይ አልሄድም። ዳንኪራ ቤት አልሄድም። ከዚህ ወጥቻለሁ! ግዜዬን ቃል በማንበብ፡ ቤትን በመንከባከብ እሳልፋለሁ።"

116 "ዉዴ፡ አሁን፡ ተመልከቺ። ችግር የለም፡ አንቺ፡ መንፈሳዊ ሰው መሆን ትችያለሽ። አሁን ግን፡ እየሽ፡ የምትሄጂበት—ቤተ ክርስትያን ልክ አይደለም። **ወደዚህኛው** ሂጂ።"

117 በፍጹም፡ ትክክል ነሽ። ያለሽበት ትክክል ነው። ይሄን የሚሰብካችሁ ሰባኪ ካገኛችሁ፡ ከእርሱ ጋር መቆየት አለባችሁ። በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ ፈልጉትና ትክክል እንደሆነ መርምሩ።

118 "እይይ፡" ይላችኋል፡ "**ወደዚህኛው** ሂጂ። እነዚህ—እንዲህ እና እንዲያ አያደርጉም። እየሽ? እዚህኛው ጋር ይሄን ነገር አያደርጉም።" መንገዱ ይህ ነው… "ችግር የለም ቀጥይበት።" ነገር ግን ከዚያች ምድር እንድትወጡ አይፈልግም። ዲያቢሎስ የሚያደርገው እንደዚህ ነው። ዓለምን ወደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አምጡላት፡ ከዓለም ነገሮች እንድትወጡ አይፈልጋችሁም።

119 ባለፈው ቀን፡ መንገድ ላይ ሰወርድ፡ ሬዲዮዬን ከፈትኩ። እና አንድ—አንድ ዜማ ነበር፡ እና ማዳመጥ ቀጠልኩ፡ እና ዜማው፡ መንፈሳዊ ዝማሬ መሆኑን ለማወቅ፡ መዝሙሩን ለመጨረስ፡ ትንሽ ቀረኝ፡ ወይም ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን ነገር ወደ ዓለም ደረጃ ለማውረድ እየሞከረ ነው። እግዚአብሔር ይማራቸው! እንዲህ አታድርጉ!

120 ኤልቪስ ፕሬስሊ ከነዚህ ጥሩ መንፈሳዊ መዝሙሮች ሁሉ፡ ስንት ያህሉ አልበሞች እንደጻፈ አይገደኝም። አሁንም በዲያብሎስ የተያዘ ሰው ነው። ብዙ ልጆችን ወደ ሲኦል ሸኝቷል፡ በዚህ ዘመን በዓለም የማውቃቸው፡ እንቅስቃሴዎች ሁሉ። ፓት ቡን እና ሌሎቻቸው፡ እሱ የቸርች ኦፍ ክራይስ አባል፣ ኤልቪስ ፕረስሊ፡ የጴንጤቆስጣል ናቸው፣ በእነዚህ ሰዎች ምሳሌ ውስጥ፡ የአስቆርቱ ይሁዳዎች ናቸው። ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን ከፍ ያሉ ነገሮች በማምጣት፡ **እዚህ** በምድር ካሉ ነገሮች ጋር ሚክስ ለማድረግ እየጣረ ነው። ህዝቡ **ከዚህ** በላይ ማየት አይችልም። **እዚህ** ያለውን ነገር ብቻ አይተው፦ "ችግር የለም፡ ያው ነው፡" ይላሉ። ያው አይደለም። ከዚያ ምድር ውጡ።

121 "ለጥቂት ቀናት ብቻ ሂዱ። ሂዱና፡ ከምድሪቱ አትውጡ፡" አላቸው። አዎን፡ እንደሚመለሱ ያውቃል። ከዚያም ይህ እንደማይሠራ ስላወቀ የተለየ ነገር አሰበ። እንዲህ አለ፦ "የምታደርጉትን እኔ እነግራችኋለሁ። ወደምትፈልጉት ቦታ ሂዱ፡ ነገር ግን ሚስቶቻችሁ፣ ልጆቻችሁ፣ ከብቶቻችሁ ሁሉ፣ **እዚህ** ትታችሁ ትሄዳላችሁ። እዚህ ትታችኋቸው፡ ትሄዳላችሁ።" ምክንያቱ፡ ወደኋላ እንዲመለሱ የሚያማልላቸው ርስት፡ እንዳላቸው ያውቃልና።

122 ዲያብሎስም የሚላችሁ ይህ ነው። አንዳንድ የአለም ነገሮች በላያችሁ ላይ አንጠልጥሎ እስካሰቀረ ድረስ፡ ዲያብሎስ እንደሚፈልገው፡ አሁንም ማጨስ ትፈልጋላችሁ፣ መጠጣት ትፈልጋላችሁ፣ እንደ አለም መልበስ ትፈልጋላችሁ።

123 ባክ ስለማድረግ ብዙ እሰማለሁ። ሰዎች ባክ ማድረግ አለ እንደሚሉት አለ ብየ አላምንም። ጉዳዩ፡ ወደ ግብጽ እንዲመለሱ የሚያማልል ብዙ ርስት

ትተው ስለወጡ ነው። ባክ ማድረግ ሰዎች እንደሚሉት አይደለም። ወደ ኋላ የሚጎትትህ፡ የዓለም ብዙ ነገሮች አንጠባጥበህ ስለወጣህ ነው።

124 ወንድም፡ እልሃለሁ፡ እስራኤል በመንፈቀ ሌሊት፡ በተዘጋጀች ጊዜ፣ በዚህ ዓለም ያላቸውን ሁሉ አጭቀው፡ ለመሄድ ተዘጋጁ።

125 እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት መነቃቃት ይላክልን። ሁሉንም ነገር አጭቀን፡ ለመሄድ እንዘጋጅ። "ወጥታችሁ ተቀበሉት፡" የሚል የእኩለ ሌሊት ጩኸት እየቀረበ ነው። ሁሉንም ነገር ብታሸጉ ይሻላችኋል። በዚህ አለም፡ ወደኋላ የሚመልሰህ፡ እና የሚጎትትህ ምንም አይነት ገመድ፡ ባይኖር ይሻልሃል። እንዘጋጅ። እየሄድን ነው። አሽጉ።

126 ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እላችኋለሁ፡ ፈርዖን በመንፈቀ ሌሊት እጅግ እስኪደነቅ ድረስ ለእግዚአብሔር ታመኑ፣ "ዉጡ! ዉጡ፡ እና ሂዱ። ያላችሁ ሁሉ ሰብስባችሁ፡ ሂዱ!" አላቸው፡

127 ዲያቢሎስ የሚሰራውን እስከማያውቅ ድረስ፡ ሰው ወደ እግዚአብሔር በጣም ቅርብ ሆኖ መኖር እንደሚችል ሳውቅ ደስ ይለኛል። ትክክል ነው። ውጣ! ሂድ! እግዚአብሔርን ታዘዝ!

128 በእምነት የተሰፋውን ቃል አየ። ጭቃ አብኩ፣ ወይም ጭቃ አብኩ ሳይሆን፡ ዕጣውን በጌታ ከተናቁ ጥቂቶች ጋር አደረገ። ፈርዖንም "ያላችሁን ሁሉ ይዛችሁ ከዚህ ውጡ! ከእናንተ ጋር ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡" አለ። ሙሴ በእምነት፡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር።

129 ለእግዚአብሔር ታማኝ ከሆንክ፡ እምነት ተአምራትን ያደርጋል። በእምነት፡ እናየዋለን።

የእኛ ጊዜ አልቋል፡ ጊዜው አልፏል።

130 ነገር ግን፣ በእምነት፣ ዛሬ ጠዋት፣ አይኖቻችሁን አንሡ። በዙሪያህ ያለውን፡ ይህን ዘመናዊ ዓለም አትመልከት፡ ነገር ግን ተሰፋ ቃል የሰጠን እርሱን ተመልከት። መጽሐፍ ቅዱስ "አሁን ሁሉንም ነገር በትክክል አናይም፡ ነገር ግን ኢየሱስን እናየዋለን፡" ይላል። ዛሬ ጠዋት፡ እርሱን አይታችኋልና፡ መንገዳችሁ ይለወጣል።

131 ለጸሎት ቃል፡ ለአፍታ፡ አንገታችንን ዝቅ እንዳደረግን። ጌታ መልእክቱ ላይ በረከቱ ይጨምርበት።

132 አሁን በልባችሁ አሰቡ። በእምነት፡ ኢየሱስን አይታችኋልን? ወይስ የዓለምን ነገሮች እያያችሁ ናችሁን? የሚታያችሁ ታዋቂ መሆናችሁን፡ ቤተ ክርስትያናችሁን ነውን? በዓለም ማሕበረሰብ ያላችሁ ተቀባይነት ነውን? ወይስ፡ በመከራ አልፎ፡ እራሱን፡ ከፍ ባለው ሰፍራ በልዑል ግርማ ቀኝ ያኖረ፡ በሰማዕትነት የተሰቃየውን፡ ለበዳዮቹ ጻድቅ የሆነውን ኢየሱስን ታያላችሁን? ዓይናችሁን አንሥታችሁ ያንን የሕይወት ዛፍ ማየት አትችልምን? እንግዲያውስ፡ የሳይንስ እና የዕውቀት ዛፍ ትታችሁ፡ ለእርሱ ተገዙ።

133 ከመጸለዬ በፊት በጸሎት መታወስ ትፈልጋላችሁ? ለምትፈልጉት ለማንኛውም ጥያቄ፡ እጆቻችሁን አንሱ። እግዚአብሄር ይባርካችሁ። እሱ እጆቻችሁን ያያል።

134 ኃጢአተኛ ከሆንክ፡ ዓይንህን አንሥተህ ተመልከት። ግድየለሽ ከሆንክ፣ ትንሽ ጭቅጭቅ እና ትናንሽ ነገሮች ካሉብህ፣ እሰኪ ምን ልዩነት አለው? አንድ ቀን መሞትህ ላይቀር። በየትኛው ቀን? ምናልባት ዛሬ! አታውቅም። ከአንድ ሰአት በኋላ በገሃነም ውስጥ ልትገኝ ትችላለህ፡ ወይም በገነት ውስጥ ልትሆን ትችላለህ። ግን አሁን መምረጥ አለብህ። በህይወትህ ውስጥ ትክክል ያልሆነ ነገር ካለ፡ አሁን የምትመርጠው፡ በእምነት ነው።

135 እንዲህ በሉ፦ "ብቻ፥ ከእሷ ጋር ከተሰማማሁ! ከእሱ ጋር ከተሰማማሁ!" ምንም ቢያደርጓችሁ፡ ሕይወትን ምረጡ። ሕይወትን ምረጥ።

136 ምክንያቱም ኢየሱስ ሲናገር፦ "ለሰው ሁሉ ኃጢአቱን ከልብ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁም ይቅር አይላችሁም።" ስለዚህ ይህን ጉዳይ ዝጉት። በልብህ ውስጥ በማንኛውም ሰው ላይ አንድ ነገር ካለብህ፣ ኃጢአተኛም ወይም ከቅዱሳን፣ በገሃነም እሳት አደጋ ውስጥ ነህ።

137 አሁን አይኖቻችሁን አንሡ። ምን ታያላችሁ፡ ጠላታችሁ? ወይስ፡ አዳኛችሁን ታያላችሁ? ዛሬ ማለዳ ምን እያያችሁ ነው?

138 ታመህ ከሆንክ፡ ዶክተርህ፡ መዳን አትችልም ብሎህ ከሆነ፡ ስለ መተላለፋችን ወደ ደቀቀበት፡ በመገረፉ ቁስል ወደ ተፈወስንበት፡ ወደ መሰቀሉ አይኖችህን አንሣ። ዶክተሩ የሚናገረውን አትመልከት፡ እሱ በሳይንስ የሚሰራ ነው። እምነት በመንፈስ እና በእግዚአብሔር አድማስ ውስጥ ይሰራል። እጆችዎን ወደ ላይ እንደተነሡ እግዚአብሄር አይቷቸዋል። አሁን እነዚህን ነገሮች እናሰብ።

እንጸልይ።

139 የዘላለም አምላክ ሆይ፣ መልእክቱ ከተነገረ በኋላ፡ ባለው በዚህ የጸጥታ አምልኮ፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህ የቃልህ ዘሮች፡ በጭንጫ ላይ አይውደቁ። ጌታ ሆይ፡ መልዕክቱ፡ በእሾህ እና በአመኬላ አይውደቅ፣ (ልክ እንደ ሎጥ) የምድር አሳብ አይነቀው፡ መጨረሻውም፡ መጣል አይሁን። ነገር ግን፡ ቅዱስ አምላክ ሆይ፡ በመልካም፡ እና በለም መሬት፡ ንሰሐ በሚገቡ ልቦች ላይ ይውደቅ። ጌታ ሆይ፡ በእኔ ላይ፡ ደግሞ ይውደቅ፡ ሁላችንም በእግዚአብሔር እይታ መሰታወት እንድንመለከት፣ የተጠላችው የጌታ ኢየሱስ ቤተክርሰትያን፡ እና የተጠላው ህዝብ፣ የተናቀውን መንገድ፡ ማየት እንድንችል፡ በዚህ በከበረ መንገድ እንመላለስ።

140 እንደ ሙሴ፡ የት እንደሚሄድ አላወቀም። ህዝቡ የት እንደሚሄዱ አላወቁም። የትኛውን መንገድ መሄድ እንዳለባቸው አላወቁም። ዝም ብለው ጀመሩ።

141 እና ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ የሚያምር ዜማ ሲዘመር፡ በእምነት፡ ያቺን ምድር በሩቅ እናያለን። አሁን እንዲህ ይሁን፡ እዚህ ያሉ ወንዶች እና ሴቶች ዓለም ምን እንደሚላቸው፡ ወይም እንዴት እንደሚሄዱ አያሰቡ። በመንፈሳቸው ተቀጣጥለው ይሂዱ።

142 ሙሴ ብርሃኑን ተከትሏል፡ እርሱም ወደ ተሰፋይቱ ምድር መራው። ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ ግን፡ ዝም ብሎ ከቀን ይልቅ ወደ ሚያምር ምድር፡ በብርሃን ተመላለሰ።

143 ጌታ፡ ሆይ፡ ዛሬ፡ ብዙዎች እዚህ ቤተ ክርስቲያን በኩር የሆኑትን፡ ክርስቶስ የተቀበሉ አዲስ የተወለዱ ሕፃናት፣ በቅዱሳት-መጻሕፍት ብርሃን፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ኅብረት፡ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲመላለሱ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ፡ በመንፈስ እንዲመሩ ስጠን። በዚህ ኅብረት፡ በአንድነት፡ በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ዙሪያ፡ መሞቱን፣ መቀበሩን፣ ትንሳዔውን ለመታዘዝ፡ በጥምቀት እያገለገልነው እንድንመላለስ። በትእዛዙ እንድናገለግለው፦ "ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ።" በመለኮታዊ ፈውስ፣ ለታመሙት እየጸለይን እንድናገለግለው። በኅብረት፣ እንጀራ በመቁረስ፣ በትሑት ልብ፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመመሥረት እንድናገለግለው። ምድር ማየት እስክትችል ድረስ፡ በመለኰታዊ ትዕዛዛት እንድናገለግለው። ስጠን፡ ጌታ ሆይ። አሁን ሁሉንም ለአንተ ሰጠን፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ ጸሎታችንን ስማ።

144 አሁን ጭንቅላታችንን ደፍተን፣ በጸጥታ፣ በዝግታ፣ ይህን ዝማሬ እንዘምር። አሁን አምልኮ ነው። መልዕክቱ አልቋል። ተረጋግታችሁ ቆዩ። ማንም አይውጣ። እናምልክ።

145 መልዕክቱ የሚያርም እርማት ነው። ያደረጋችሁትን፣ ምን ማድረግ እንደነበረባችሁ፣ ዛሬስ እንደ ዛሬ እንድትሆኑ ያደረጋችሁ ነገር አሰቡት። ዛሬ እንድትኮንኑ የሚያደርጋችሁ ትናንት የሆነ ነገር ስላደረጋችሁ ነው። ነገ ምን ይሆን? ዛሬን አስተካክሉ፣ ነገ ነጻ ትሆናላችሁ። አያችሁ? ምርጫ ማድረግ አለባችሁ። የምትመርጡት እንዴት ነው? "በእምነት፡ አሁን ሁሉንም ነገር ፈታሁ። አሁን ፈታሁት፣ ስለዚህ አንድ ቀን ወደዚያ እሻገራለሁ።"

> በዚያ በድንቅ አገር፡
> በውብ ዳር እንገናኛለን-...

አሁን ጌታን በመንፈሳችሁ አምልኩት።

> በዚያ በድንቅ አገር፡

የተናቀች ቤተክርስቲያንን እናገኛታለን። ከባድ ጉዞ ነው፣ ግን አንድ ቀን እንገናኛለን።

> ለባለ ጸጋው አምላካችን፡
> ምስጋናችንን እናቀርባለን፡
> ለታላቅ የፍቅር ስጦታው፡
> ስለማ'ይለን ጸጋው...

ስለ ጌታ ከተናቁት ጥቂቶች ጋር፣ በእምነት፣ እኔ እመርጣለሁ።

> በዚያ በድንቅ (በዚያ በድንቅ) አገር... (አገር)
> በውብ ዳር እንገናኛለን፡ (አገር)
> በዚያ በድንቅ (በዚያ በድንቅ) አገር፡
> በውብ ዳር እንገናኛለን፡
>
> በምታምረው ያቺ አገር...

እሱን ብቻ አምልኩ። አምልኮው ነው።

> በእምነት... የምናያት፡

በእምነት ምርጫዬን አደርጋለሁ።

አባታችን በዚያ ይሆናል…

146 እነ ወንድም ጆርጅ፣ እነ ወንድም ሴዋርድ፣ የጌታ የሆኑትን ቅዱሳን ሁሉ፡ እዚያ አያለሁ።

… ይሆናል መኖርያም ያዘጋጅልናል። (አዎን፡ ጌታ ሆይ!)
ድንቅ…

147 አባቷ፣ ሃዋርድ፣ ኤድዋርድ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት፣ ያቺን መንገድ የተቀበሉ፡ የቀደሙት ቅዱሳን ወገኖች ሁሉ።

በዚያ በድንቅ አገር (አዎን፡ ጌታ ሆይ!) አገር (አገር)፡
በውብ ዳር እንገናኛለን።

በዚያኙ ውብ ላይ እንዘምራለን-… (አምላክ ሆይ!)
ልንዘምር የቅዱሳንን ግሩም መዝሙር፡ (ክብር ለእግዚ
አብሔር!)
… መንፈሳችንም ከቶ አያዝንም፡
በዚያ የእረፍት ቦታ በረከት እንጂ ማልቀስ የለም።

በዚያ ድንቅ፡ ድንቅ አገር… (አገር)
በውብ ዳር እንገናኛለን-…

**ሙሴ፡ በእምነት** AMH58-0720M

(By Faith, Moses)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሐምሌ 20፡ 1958 እሁድ፡ ጠዋት፡ በዩ/ኤሰ/ኤ፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ከሚገኝ ብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org